# …ሁሉንም ነገር ሽብርተኛነት? ወይስ ሁሉንም ነገር በሽብርተኝነት?

ሁናቸው አማኑ

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ሚያዚያ 19/2004 በወጣው ፍትህ ጋዜጣ ስለ አገር ትርጓሜ በቃላት ተጠብበዋል፤ አገር የብዙ ነገር ድምር ውጤት መሆኗን ለማብራራት ሰፊ ገለፃም ሰጥተዋል፡፡ ‹‹ኢትዮጵያዊነት እንደ እጣን በሚመዘዝ ጭስ ሙስሊሙን ከክርስቲያኑ የሚያስተሳስርና እኩል የሚያዋህድ፣ በወንዝ፣ ተራራና ሸለቆ የሚገናኝ ወዘተ… የሚል ቃና ባለው ያማረ ቃላትም ነው የሀገርን ትርጉም አስረግጠው ሊያብራሩና ሊገልፁ የሞከሩት፡፡

ፕሮፌሰሩ ይህን በብዙና ባማረ ቃላት የተዋበ ነገር የተናገሩት ኢትዮጵያዊነት ህብር ነው፣ ከብሄር ብሄረሰብም በላይ ነው ለማለት ነው፡፡

የእሳቸው ደቀመዝሙር /የፍትህ ዋና አዘጋጅ/ ይህንኑ ተከትለው ኢትዮጵያዊነት ህብር እንጂ ብሄር ብሄረሰብ አይደለም ብለውናል፡፡ በነገራችን ላይ ዋና አዘጋጁ ቪዛ አግኝተው ይሁን ሌላ ‹መውጣትና መግባት› የሚሉ ቃላቶችን አብዝተዋል፡፡ ወይም የቪዛውን ጉዳይ የሚያጠናክርላቸው ኹነቶችን ለማሰባሰብ እያንዳንዱን ሀረግ ለቪዛ ትርጉም ይኖረዋል በሚል ስሌት ተርጉመው ‹እያስፈራሩን ነው፣ ውጡ እየተባልን ነው› ወዘተ… ቃላቶች አጠናክረው መጠቀም ጀምረዋል፡፡

በስም የነፃ ፕሬስ ምህዳር ላይ ሆነው የአንድ ወገን ያውም የጨፈነ ፖለቲካ አቋም ማስነገሪያ ልሳን በሆኑበት ‹‹ፈራን… ሰላም ፈራን ማለት›› ቀጥለዋል፡፡ ይልቅ መፍራትም ባይሆን ማክበር ህግን ነው፣ የመፃፍም፣ ኃሳብን በነፃ የመግለፅም መብት መነሻ የሆነውን ህገ መንግስት ነው ብሎ መናገር አሁንም ማስፈራራት አይደለም፡፡ ወደ ተነሳንበት እንመለስ፡፡

በጋዜጣዋ ስለ ሀገር ትርጓሜና ሀገር ከምን እንደተሰራች የሚነግሩን ፕሮፌሰር መስፍን ሀገር ከህግና ህጋዊነትም መሰራቷን ፈፅሞ የረሱት ይመስላል፡፡ ሀገር ወንዝ ቢኖራትም፣ አንዱን ከአንዱ በመንፈስም በስጋም የሚያስተሳስር እጣን ቢኖራትም፣ የተለያየ እምነትና አስተሳሰብ ቢኖራትም፣ ሸለቆና ተራራ ቢኖራትም፣ ፕሮፌሰር ቢኖራትም… በሁሉም ወገን የሚከበር ህግ ከሌላት ሀገር አይደለችም፡፡

ሀገር ህዝብ ቢኖራትም ሰላም ከሌላት ሀገር አይደለችም፡፡ ሀገር ሀገር እንድትሆን የግድ እንደ ታህሪር ባለ አደባባይ በየቀኑ የሚንጎማለል ህዝብ አያስፈልጋትም፡፡ ይልቅ ከመንጎማለል በተሻለ የተረጋጋ ሰላም፣ ልማትና የሚጨበጥ የማደግና የመጠቀም ራዕይ ያለው ህዝብ ነው እንዲኖራት የሚያስፈልገው፡፡ በተለይ እንደ እኛ ላለ ህዝብ ደግሞ ሀገር ለብሄርና ለማንነት ጉዳይ ቅድሚያ እውቅና ልትሰጥ ይገባታል፡፡

በከተማ ያለውንም፣ በገጠር ያለውንም ክርስቲያንና ሙስሊም፣ ባለ ሌላ እምነቱንም፣ እምነት የሌለውንም ጭምር በአንድ የኢትዮጵያዊነት ገመድ ያስተሳሰረው ነዋሪው ኢትዮጵያዊነት ባህል እንጂ እጣንና ጭሱ ወይም የነበሩ ስርዓቶች አይደሉም፡፡ የየስርዓቶቹ ባለሚሎች ሲሻቸው ክርስቲያናዊ መንግስት በማቋቋምና ሀገሪቱን በራሳቸው የእምነት መስመር ቀይደው በመምራት ሌሎች ዝቅ ብለውና የይስሙላ ኢትዮጵያዊነት ተቀብለው እንዲኖሩ አስገድደው ቆይተዋል፡፡

በወንዝና ተራራ የተጠፈረ ኢትዮጵያዊነት በሌላ አነጋገር የኃይል አንድነት ላይመለስ የፈራረሰው፣ በዴሞክራሲያዊ የመፈቃቀድ አንድነትም የተተካው ማንነትን ላከበረ ኢትዮጵያዊነት ቅድሚያ ሰጥቶ ነው፡፡ ብሄርን ያላከበረ ኢትዮጵያዊነት በስም ከመነገድ ያለፈ ፋይዳ እንደማያመጣ መረዳት ብዙ ድካም አይጠይቅም፤ ይህች በብሄር ብሄረሰቦቿ ህብር ውበትና ልዩ ልዩነት የተገነባች ሀገራችንን በመመልከት ብቻ መገንዘብ የበለጠ ይቀላል፡፡

በኢትዮጵያ ምድር ህዝብ ከህዝብ ተባልቶና ተናቁሮ አያውቅም፡፡ ይሄ ኗሪ ጨዋነታችን ነው፡፡ ወደፊትም ይህ ለብዙ ዘመናት የዳበረ የኢትዮጵያዊነት ባህሪ ይቀጥላል ብለን ማመን ትክክል ነው፡፡ የብሄርና የመደብ ጭቆና በኢትዮጵያ ተከስቶ አያውቅም የሚል ቃልና ሞራል ካለን ግን እኛ ማን ነን የሚል ጥያቄ ያስከትላል፤ የታሪክ ተመራማሪ፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች፣ ሀቀኛ ተቃዋሚ ወዘተ… ቢያንስ ይሄ አይጠፋውምና፡፡

ከልብ ሆነም ከአንገት ማንነትን ያላከበረ ኢትዮጵያዊነት ለኢትዮጵያ ህዝብ ምኑም ያለመሆኑ ማስረጃ ራሷ ፍትህ ልትሆን ትችላለች፡፡ ፍትህ በሰኔ 15 ርዕሰ አንቀጿ ይህን እውነት በተጨባጭ ገልጻልናለች፡፡ *‹…ሁሉም ትውልድ የራሱ አሻራ ያረፈበትን ታሪክ ፅፎ ያልፋል፤ አንዳንዱ የጦርነትን ሌላው ደግሞ የልማትን ገድል ይፈፅማል፡፡ የጦርነትን ገድል የፈፀሙት የአሁኖቹ ባለስልጣናት ነባሩ ትውልድ የማለባቸውን የታሪክ ኃላፊነት እና የዘመን መንፈስ መሸከማቸው ስህተት አልነበረም የሚል እምነት አለን፡፡ በጊዜው ስህተት ነው ብለው የሚያምኑት ስርዓቱ እንዳይናጋባቸው ይሰጉ የነበሩ የመንፈስ ተገዳዳሪ ባለስልጣናት እንጂ የእነዚህ አርበኞች ደጋፊ የማህበረሰብ ክፍሎች አለመሆናቸው ግልፅ ነው፡፡›*

ፍትህ በትክክል እንዳስቀመጠችው የዛሬውን ልማት፣ ጅምር ዴሞክራሲና እድገት ያስገኙልን የትላንት ባለገድሎች፣ መራሩን መስዋዕትነት የከፈሉት የብሄርና የመደብ ጭቆናዎችን በማስወገድ የህዝቦች መብት እንዲከበር ለማድረግ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት፣ እኩል ተጠቃሚነትና ነፃነት እንዲከበር ለማስቻል ነው፡፡ ይሁንና የዚህ መብት ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን ለመብቱ የታገለውና መብቱን ያስከበረው የየብሄረሰቡ ድምር ውጤት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው፡፡

በብሄሬ፣ በማንነቴ ተጨቁኛለሁ ያለውም፣ በስሜ ተነግዶብኛል እኩል ተጠቃሚ አይደለሁም ያለውም፣ የብሄርም የመደብ ጭቆናም ደርሶብኛል ያለውም ጭቁን ህዝብ መብቱን ለማስከበር ታግሏል፤ በራሱ ትግልም ከጨቋኞች ነፃ ወጥቷል፡፡ ነፃ የመውጣቱ ውጤት ብሄሩንና ማንነቱን ያከበረ ኢትዮጵያዊነት እውን ሆኖ እንዲያይ አስችሎታል፡፡

ይህ እውነታ በታሪክ ተመራማሪም፣ በሰብዓዊ መብት ተሟጋችም ወዘተ... አቅጣጫዎች ቢታይ የብዙ ሺ ዘመን ታሪክ አላት ብለን የምንኮራባት ሀገራችን የሁሉም ህዝቦች ታሪክ እየተነገረባት የኖረች አይደለችም፤ የሁሉም ህዝቦች ባህልና እምነት፣ ኃይማኖትና ወግ በእኩል ቀርቶ በጥቂት ማበላለጥ እንኳ እየተገለፀባት የመጣችም አይደለችም፡፡ ኢትዮጵያዊነታችን በጎ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ጠባሳም ያለው ነው፡፡

የሀገራችን ጀግኖች የሀገራችን በጎ ታሪክ በዓለም እንዲታወቅና ጥንት ወደነበረው ስልጣኔ ለመመለስ የሚያስችለንን የዛሬውን ስንቅና መሰረት እንዳኖሩልን ሁሉ በውስጥ ማንነታችንን /የብሄር እኩልነትና መደባዊነት/ ጉዳይ ትተው ያለፉት ጠባሳ የሚረሳ አይደለም፡፡ በንፅፅር በጎውን እያወደሱ፣ ስህተቱን እያረሙ መሄድ ተገቢ የሚሆነው ለዚህ ነው፡፡ ይህን ሃቅ ክዶ በጭፍን ማውገዝና በመጥላት አባዜ መጠመድ ምሁርም ተመራማሪም አያሰኝም፡፡

እውቀት ሀገርንና ህዝብን ማወቅ ነው፤ ገጠሩንም፣ ከተማውንም፣ በጎውንም፣ መጥፎውንም መመርመር ነው፡፡ እውቀት ልበ ብሩህነት ነው፡፡ እውቀት ሁልጊዜም መጠየቅ ነው፤ እውቀት መጥላት አይደለም፤ መፈረጅ አይደለም፣ መጨፈን አይደለም፡፡ የጨፈነ የሩቁን ብቻ ሳይሆን የስሩን አያይም፤ ስለሩቁ ብቻ ሳይሆን ስለ ቅርቡ በጎነት አይመለከትም፤ አይመዝንም፤ መጨፈን እንደ ድሮ ህንድ ፊልም ሲጀምር በምን እንደሚጨርስ ይታወቃልና ምንም ቢል አይታመንም፡፡

ስለዚህም በጭስ ብናኝ፣ በወንዝና ተራራ ከሚገለፅ ኢትዮጵያዊነት በላይ በብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትና ነፃነት፣ ዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ በህግና ህጋዊነት የታሰረ መብትና ግዴታ፣ ህገ መንግስትና ህገ መንግስታዊ ስርዓት ያስፈልገን እንደነበር ማወቅ ይገባል፡፡ ምንም እንኳ ህገ መንግስቱንና ሌሎች ህጎችን ሲመቹን ብቻ የምንጠቅሳቸው ቢሆንም በህገ መንግስቱ የተዘረዘሩ መብትና ግዴታዎችን የሚያስፈፅም አዋጅና ሌሎች ህጎችም ያስፈልጉን ነበር፡፡

ይህን የባለ ብዙ መገለጫ ኢትዮጵያዊነት መልሶ ወደ ኋላ የማይንድ ህግና ስርዓትም ያስፈልገን ነበር፡፡ በጭስም፣ በእጣንም በከርቤም የተገናኘው፣ የተዋሃደው ኢትዮጵያዊነት ያለ ህግና ስርዓት አይቀጥልምና፡፡

ህግና ስርዓት በመበላሸቱ ሶማሊያ ፈርሳ አይተናል፤ ህግና ስርዓትን ማክበርና ማስከበር ባለመቻሉ፣ ለህግ መገዛትና ለህግ ልዕልና በኃላፊነት ስሜት መንቀሳቀስ ባለመቻሉ ብዙ ሀገሮች አጓጉል ሲሆኑም ተመልክተናል፡፡

የህግ መከበር ጥያቄ የለውም፤ ህግ አውጪው ያከብረዋል፤ ህግ አስፈፃሚው ያከብረዋል፣ ህግ ተርጓሚው ያከብረዋል፣ እንደ ፓርቲ የተደራጀው ያከብረዋል፣ ጋዜጠኛ ነኝ ብሎ ራሱን የሚገልፀው ያከብረዋል፣ ባለ ሌላ ሙያውም ያከብረዋል ወዘተ…፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን የህግን መከበር ህዝብ ይፈልገዋል፡፡

የመንግስት እየተባሉ የሚጠሩት የህዝብ መገናኛ ብዙሃንም ሆኑ የግል እየተባሉ የሚጠሩ ጋዜጦች ህግን በማክበርም ሆነ ህግ እንዲከበር የየራሳቸውን ድርሻ በመወጣት ሂደት እኩል ኃላፊነት ያለባቸው ናቸው፡፡

የመንግስት ኃላፊ የሚባሉትም ሆኑ የዚህች ሀገርና ህዝብ ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ እንደ ፓርቲ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ መሪዎች አሁንም ያለባቸው ሀገራዊ ሃላፊነት ተመሳሳይ ነው፡፡ ምናልባት የኃላፊነቱ የተጠያቂነት ጉዳይ እንደ ፍርድ ቤት ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ከሌለው በቀር፡፡ እናም ከዚህ አግባብ ባፈነገጠ አኳኋን ጣት መቀሳሰሩ ነው ፕሮፌሰር መስፍን ያሉት የአዕምሮ ክስረት ሊሆን የሚችለው፡፡

የአዕምሮ ክስረት የራስን ጥልቅ ፍላጎት ገደብ በሌለው ሁኔታ ለማሳካት ሲባል ህግን መጣስ ወይም ህግን ለመጣስ መሞከር ነው፡፡ የአዕምሮ ክስረት ውስጥ የገቡ ኃላፊነት የማይሰማቸው ወገኖች የግል ፍላጎታቸውን ለማሳካት ሲሉ እስከ ሽብር በዘለቀ የጥፋት ተግባር ውስጥ ይገባሉ፡፡ በጨፈነ ፍረጃና ጥፋት ውስጥም ይታያሉ፡፡ ሀገር ህግ እንደሚያስፈልጋት ይዘነጋሉ፡፡ ህግን አክብረው

መንቀሳቀስን ይፈራሉ፡፡ በአጠቃላይ ህግ ያስፈራቸዋል፣ ለምን ቢባል ህግ የሚሰጠውን መብት ያህል የሚጥለው ግዴታ አለና፡፡

ለእንደነዚህ አይነት ወገኖች ህግ ስጋት መሆኑ አይገርምም፣ ህግ ካለ ስርዓት አለ፣ ስርዓት ካለ ደንብ አለ፣ በተቀመጠው ደንብ የማይጓዝ ወገን የህግ ተጠያቂነት ያርፍበታል፣ ወይም በህግ አግባብ እንዲሄድ ይገደዳል፣ ይህ ገደብ ለስርዓት አልበኞች አይመችም፡፡

ስለዚህም የህግና ህጋዊነትን ትርጉም እያዛቡ ከራስ ፍላጎትና እምነት ጋር የማያያዝ ሂደት ይከሰታል፣ ፕሮፌሰር መስፍን ‹‹የአዕምሮ ክስረት ሁሉንም ነገር ሽብርተኛነት?›› ብለው ‹...ሁሉንም ነገር በሽብርተኝነት› ለማለት እንዳልፈቀዱት፣ የእጣንና ከርቤን የማዋሃድ ትስስር አስረድተው የብሄር ብሄረሰቦችን ልዩ ልዩነትና ማንነት ጉዳይ እንዳቀለሉት፡፡ የአዕምሮ ክስረት ሁሉንም ነገር ሽብርተኛነት ወይስ ሁሉንም ነገር በሽብርተኝነት?...